# ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ብትሆን ምን ጥቅም ታገኛለች ?

## መግቢያ

በጥር ወር 1995 ዓ.ም ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል እንድትሆን የኢህአዴግ መንግስት እንዳመለከተና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቅድመ-ሁኔታዎችን ለሟሟላት ሽር-ጉድ እን ደሚባል ይታወሳል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ አባል ብትሆን የምትጎዳው ነገር የለም ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ይበልጣል በሚል የኢህአዴግን ጥድፊያ የሚቃወሙ ኃይሎች ጋር የጦፈ ውይይት እንደሚካሄድ ይታወቃል። ከኢንፎርሜሽን እጥረት የተነሳ ውይይቱ የቱን ያህል ሳይንሳዊና በቲዎሪ እንዲሁም በተግባራዊ ጥናት ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ለመገመት ፣ የየትኛው ወገን አቀራረብ አስተማማኝና እንዲሁም የሚያሳምን መሆኑን ሙሉ በሙሉ እንደዚህ ነው ብሎ ለመናገር ቢያዳግትም ፣ በተለይም ከተቃዋሚው ወገን የሚቀርበው ትችት የሚደገፍ መሆኑን ከመጀመሪያወኑ ማረጋገጥ ይቻላል።

ይህ ጸሀፊ ከዚህ ቀደም ነፃ ገበያን አስታኮ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አማካይነት በአገራችን ምድር በተግባር የተመነዘረውን ፖሊሲና ያመጣውን አሉታዊ ውጤት በጦቢያና በተለያዩ ዌብ ሳይቶች ላይ ለህትመት አቅርቦ መነጋገሪያ ሊሆን በቅቷል። በተለይም የመንግስትን ባንክ ለውጭ ከበርቴዎች ለመሸጥ የተደረገውን ኢ-ሳይንሳዊና አገር አፍራሽ እርምጃ በመቃወም አንድ ውጤት አግኝቷል። የመንግስት ባንኮች ለውጭ ነጋዴዎች አለመሸጣቸውን  በቅርብ ተከታትሏል። በሌላ ወገን ግን የመንግስትም ሆነ የግል ባንኮች ስራቸው ያልተቀላጠፈ ብቻ ሳይሆን ወደ አስራ ሰባት ቢሊዮን የኢትየጵያ ብር ላይ ተቀምጠው የምርት እንቅስቃሴ ፣ የስራ-ክፍፍል ዕድገት ፣ የንግድ ክንውን ፣ በአጠቃላይ የውስጥ ገበያ(Home Market) እንዳይዳብር እንቅፋት እንደሆኑ ለመገመት ይቻላል። የባንክን አሰራር ቀልጣፋ የሚያደርግና ፣ ባንክ እራሱ ጠቅላላው አሰራሩ ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር እንዲያያዝ የሚያደርግ ሰፋ ያለ ህግ እስካልወጣ ድረስ ይህ ሁኔታ በዚህ እንደሚቀጥልና የአገሪቱ ኢኮኖሚ እዚያው በዚያው እንደሚታሽ መታወቅ አለበት።

በኢህአዴግ መንግስት በኩል አሁንም እንደቀድሞው ካለምንም ሳይንሳዊ ጥናት ኢትዮጵያን የግሎባል ካፒታሊዝም መጨፈሪያ ለማድረግና ኢኮኖሚዋ በአጠቃላይ እዚያው በዚያው እንዲተራመስና ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዳይዳብር ብሎም ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰብአዊ መተሳሰር እንዳይኖር የሚደረገው ውጣ ውረድ እጅግ አደገኛ መሆኑን ለማመልከት ይሞከራል። እንደሌሎች ቀደም ብለው እንደወጡትና ተግባራዊ እንደሆኑት ፖሊሲዎች ሁሉ የአገሪቱን ህገ-መንግስት የሚፃረሩ ተደራቢ አገር አፍራሽ ፖሊሲዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የሁለትና የሶስት ትውልድ ወንጀል እንደመፈጸም ይቆጠራል። ማን ኛውም መንግስት ወደ አንድ እርምጃ ከማምራቱ በፊት ፖሊሲው ከአገሪቱ ህገ-መንግስት ፣ ጥቅምና እንዲሁም ከታሪክ ጋር የተገናዘበ ፣ በተለይም ከማዕከለኛም ሆነ ከረጅም ጊዜ አንፃር ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመጣውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት በበቂው ማጥናትና ማጤን ይኖርበታል።የመንግስትን ፖሊሲ የሚፃረሩ ከህዝቡ ውስጥ የሚሰነዘሩትን ትችቶች ሆን ብሎ ማደመጥና ፈጥኖ እርምጃን ከመውሰድ መቆጠብ ያስፈልጋል። መንግስት የህዝብ አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ወክልሀለሁ ያለውን ህዝብ ብሶትና ጩኸት በየጊዜው ማዳመጥ አለበት። ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ሳትሆን ያገኘችው ጥቅም ምንም ነገር

የለም ብሎ ወደ መደምደሚያ ላይ መድረስና ከተቃዋሚው ኃይል በኩል የሚሰነዘረውን ትችት ለማጣጣል መመከር ያለዋቂነትን ነው የሚያሳየው።

ከዚህ በመነሳት ፣ ይህ ጸሀፊ እንደተለመደው በመጀመሪያ የዓለም ንግድ ድርጅትን ታሪካዊ አመጣጥና ሚናውን በማሳየት ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ብትሆን በተለይም የእርሻው መስክ እንደሚጎዳና አገራችን የበለጠ ህዝባዊ ትርምስና ድህነትን እንደምትጎናጸፍ ለማመልከት ይሞክራል። በተለይም ለአንድ አገር ዕድገት እንደ ኢትዮጵያ ያለች ገና በድህነት የምትማቅቅ አገር እራሷን ነፃ ለማውጣት በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ የኢንዱስትሪ አብዮትና የውስጥ ገበያ ማካሄድ እንዳለባት በዝርዝር ለማቅረብ ይሞክራል። ካለዚህ መሰረትና የውስጥ ገበያ ሳይዳብር አገራችንን የቻይናና የሌሎች ካፒታሊስት አገሮች ሸቀጣ ሸቀጥ ማራገፊያ ለማድረግ መሯሯጥ የድህነታችንን ዘመን ለብዙ ዐመታት ያራዝመዋል። ከዚህ በመነሳት ለአገራቸው ዕደገት ፣ ሰላምና ብልጽግና እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች ሁሉ የዚህን እርምጃ ጉዳት በማጤን በህገ-መንግስት የተደነገገላቸውን መብት የማስከበር ዲሞክራሲያዊ መርሆ ተገን በማድረግ ፖሊሲው እንዲከሽፍ ያልተቆጠበ ትግል ማድረግ አለባቸው።

## <u>የዓለም ንግድ ድርጅት ታሪካዊ አመጣጥና ሚና</u>

ዛሬ የዓለም ንግድ ድርጅት በመባል የሚታወቀው የተመሰረተው እ.አ.አ በ1948 ዓ.ም ሲሆን ፣ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ብቅ ያለውን የኃይል አሰላለፍ ያንፀባርቃል። እን ደሚታወቀው ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፍጻሜ ጀምሮ የተከሰተው አዲስ የኃይል አሰላለፍ የዓለምን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስክ በአዲስ መልክ መዘጋጀት እንዳለበት አመነ። ይህ በአሜሪካ የሚመራው አዲስ የኃይል አሰላለፍ ከዚህ ቀደም የዳበረውንና እ.አ.አ ከ1929 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1945 ዓ.ም እየተዳከመ የመጣውን የስራ ክፍፍልና የንግድ ልውውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ንግድን ለማስፋፋትና ሀብትን ከበለጸጉ አገሮች በዕድገታቸው ኋላ ወደቀሩ አገሮች ለማንሸራሸር በሚል ሽፋን ስር በአዲስ መልክ መደራጀት እንዳለበት ተገነዘበ። በመጀመሪያ እ.አ.አ በ1944 ዓ.ም ሁለቱ እህትማማች ድርጅቶች ፣ የዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አሜሪካን አገር በብሬተን ውድስ ከተማ ሲመሰረቱ ፣ እ.አ.አ በ1948 ዓ.ም አጠቃላይ የንግድና የታሪፍ ስምምነት(General Agreement on Trade & Tarif) እ.አ.አ ከ 1994 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የዓለም የንግድ ድርጅት(WTO) ተብሎ በመጠራት የሚታወቅ 23 አገሮችን ያቀፈ ድርጅት ይመሰረታል። ዛሬ የንግድ ድርጅቱ አባላት በጠቅላላው 123 አገሮች ናቸው። በጊዜው ከደቡቡ የዓለም አቀፍ ክፍል አስራ አንድ የሚሆኑ በዕድገታቸው ወደ ፊት ያልገፉ አገሮች አባል ይሆናሉ። በእነዚህ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በተመሰረቱት ድርጅቶች መሀከል ግልጽ የሆነ የስራ ክፍፍል ሲኖር ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሶስቱም ድርጅቶች የሚመሩበት የርዕዮተ-ዓለምና የቲዎሪ መሰረት በእነ አዳም ስሚዝ ፣ ከ1880 ዓ.ም ጀምሮ ኒዎ-ሊበራሊዝም በመባል የሚታወቀውንና በ1940ዎችና በ1950 ዓ.ም ጀምሮ እየረቀቀና እየዳበረ የመጣውን በዓለም አቀፍ ደረጃ የስራ ክፍፍልንና የንግድ ልውውጥን ጠቃሚነት የሚያምንና በሚሰብክ ዕውቀት መሰረት የተደገፈ ነው። በሌላ አነጋገር ፣ በዘመነ ቅኝ-ግዛት አገዛዝ የሰፈነውን ፣ ሶስተኛው ዓለም አገሮችን ከመሬት ውስጥ በሚገኝ ጥሬ-ሀበትና በእርሻ ምርት ላይ ቢያተኩሩና ቢሰለጥኑ ወደ ዕድገት ሊያመሩ ይችላሉ የሚለውን ቲዎሪ ከአዲሱ ዓለም አቀፋዊ የኃይል አሰላለፍ ጋር በማቀናጀት እነዚህን አገሮች የበለጠ ጥገኛ ለማድረግና ኢኮኖሚያቸውንና ሀብረተሰብአዊ አወቃቀራቸውን ለመቆጣጠር እንዲያመች ሆን ብሎ የተቀነባበረ ፍልስፍና ነው።

የነገሮችን አቀማመጥ ይበልጥ ለመረዳት በሶስቱ መሀከል ያለውን የስራ ክፍፍል መጥቀሱ ጠቃሚ ይመስለል። ዓለም ባንክ ሲቋቋም ዓላማው በመንገድ ስራና ትናንሽ ፕሮጀክቶች ላይ ሲያተኩር ፣ ይበልጥ የገንዘብና የቴክኒካል ድጋፍ ይሰጥ የነበረውና ያለው ወደ ውስጥ በሳይን ስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ ዕድገትን ማምጣት አልነበረም። አይደለምም። በፖሊሲው መሰረት በዓለም ባንክ አማካይነት ወደ ሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚገቡት

ርዳታዎች ያለቀላቸው ተጨባጭና የቴክኒካልና የሃሳብ "ርዳታዎች" እንጂ እዚያው በየአገሮቹ በሳይንስ ምርምር ከብዙ ልምድና ሙከራ በኋላ የዳበረ ድጋፍ አይደለም። ይህ ዐይነቱ ድጋፍ ተግባራዊ እንዲሆን ወይም ደግሞ አንድ የሶስተኛው ዓለም አገር ርዳታውን ለማግኘት በዓለም ባንኩ የተደነገገውን የአሰራር ስልትና ፍልስፍና መከተል አለባት። ርዳታው ርዳታ ይባል እንጂ በብድር መልክ የሚመጣ በመሆኑ ርዳታውን የምትቀበለው አገር ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ምርቶችና ዝቅተኛ ተጨማሪ ምርት( very low value added) ባላቸው የእርሻ ውጤቶች ላይ ማትኮር አለባት። ዛሬ የዓለምን የኢኮኖሚ መዛባትና በተለይም ደግሞ የብዙ አፍሪቃ አገሮችን የኢኮኖሚ መክስከስና ህብረተሰብአዊ ዝብርቅርቅነትና ወደ እርስ በርስ ጦርነት ማምራት ስንመረምር የምናገኘው መልስ የዓለም ባንክ ርዳታ የቱን ያህል ለብዙ የአፍሪቃና ለሌሎች የሶስተኛው ዓለም አገሮች ኢኮኖሚ ድቀትና ድህነት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳደረገ መገንዘቡ ቀላል አይሆንም። የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅትንም የስራ ድረሻ ስን መለከት ፣ጊዜያዊ አጠቃላይ የንግድ ሚዛንን መዛባት ለማረምና ለመደጎም ቢሆንም ወደ የአገሮች አጠቃላይ ኢኮኖሚ ፖሊሲያቸው ውስጥ ጣልቃ በመግባት የገንዘብ እንቅስቃሴ እን ዲገደብና ርዳታውን ለማግኘት የሚሹ አገሮች በተወሰኑ ምርቶች ላይ ብቻ በማትኮር ሀብት ከውስጥ ወደ ኢንዱስትሪ አገሮች እንዲፈስ በማድረግ የባሰ ኢኮኖሚያዊ መዘበራረቅንና የሀብት ሽግሽግን በማፋጠን በየአገሮች ውስጥ በደሀና በሀብታም መሀከል ያለው ልዩነት ይበልጥ እየሰፋ እንዲመጣ ያደረገ ነው። በስመ ነፃ-ንግድ አማካይነት የአንድ አገር ገበያ ለውጭ ሸቀጣ ሸቀጥ ማራገፊያ ክፍት ሲሆን ወደ ውስጥ የህዝቡ የማምረት ኃይል እንዲደቅና የስራ ክፍፍል እንዳይዳብር ያደረገ እጅግ መርዘኛ ፖሊሲ ነው። ወደ ዓለም ንግድ ድርጅት ስንመጣ ከማዕከለኛም ሆነ ከረጅም ጊዜ አንፃር የየአገሮችን ገበያ ሙሉ በሙሉ ልቅ በማድረግ ምርትና አገልግሎት ካለምንም ገደብ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱበትን መሰረት ለመጣል ነው። እንደሁለቱ እህትማማች ድርጅቶችም ፣ የዓለም አቀፍ ንግድ ደርጅት ፍልስፍና በዚህ ዐይነት የንግድና የአገልግሎት ልውውጥ በደሀ አገሮችና በኢንዱስትሪ አገሮች መሀከል ያለው የዕድገት መዛባት ሲስተካከል ቀስ በቀስ በእርግጥ ደግሞ በሁሉም አገሮች ያሉ ህዘቦች በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ የሚመረተው የምርትና የአገልግሎት ውጤት ተካፋይ በመሆን ደስታን ይጎናጸፋሉ ይለናል። ይህ የንግድ ድርጅቱ ፍልስፍና ተግባራዊ መሆኑን ለመረዳት ወደ አንዳንድ መሰረተ ሀሳቦች ጠለቅ ብለን እንግባ።

ወደ ዛሬው አጠቃላይ የነፃ-ንግድ ልውውጥና በአባል አገሮች መሀከል ገበያውን ሙሉ በሙሉ ልቅ ማድረግ ያስፈልጋል ወደ ሚለው መደምደሚያ ከመደረሱ በፊት ፣ የመጀመሪያው የዓለም ንግድ ድርጅት ውይይትና ስምምነት ያተኮረው በኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች ላይ ሲሆን ፣ ይህም ከውጭ ወደ ውስጥ በሚገቡ ምርቶች ላይ የሚጣለውን ከፍተኛ ቀረጥ መቀነስ ነበር። ድርጅቱ ከተቋቋመ ጀምሮ እ.እ.አ እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ የኬኔዲ ውይይት ወይም ዙሪያ(Kennedy round) ውይይቱና ስምምነቱ አብዛኛውን ጊዜ በራሳቸው በኢንዱስትሪ አገሮች መሀከል የተካሄደ ሲሆን ፣ ታሪፍን በመቀነስ በኩል ውጤት ላይ ተደርሷል። እ.እ.አ እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ በአብዛኛዎቹ ምርቶች ላይ የታሪፍ ቅነሳ ሲጠናቀቅ ፣ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ የተከሰተው ልዩ ዐይነት የኢኮኖሚ ቀውስና የዘይት ዋጋ መናር ውይይቱን አጠቃላይና የጠለቀ እንዲሆን አደረገው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለይም ታሪፍ-ነክ ባልሆኑ የንግድ ልውውጥን በሚያደናቅፉ መሰረተ ሃሳቦች ላይ መወያየትና ስምምነት መድረስ አስፈላጊ መሆኑ ታመነበት። እነዚህም ፣ የየመንግስታትን የውስጥ ፖሊሲ የሚመለከቱ ሲሆን ፣ ለኢን ዱስትሪዎች እንቅስቃሴ የሚሰጠውን ድጎማ ፣ ወደ ውጭ በሚላከው ዕቃ ላይ የሚደረገውን ልዩ ድጋፍና(Export subsidy & Credits) እንዲሁም ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ንግድን ያደናቅፋሉ ተብለው የሚገመቱ ህጎችንና ስርዓቶችን ማስወገድ ነበር። ይህ ውይይት ከረጅም ዐመታት በኋላ እ.እ.አ በ1979 ዓ.ም ስምምነት ይደረስበታል። እ.እ.አ ከ1986 ጀምሮ እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ኡራጋይ ዙሪያ(Uruguay Round) የተደረገው ውይይትና ስምምነት የዓለም ንግድ ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ እራሱን የቻለ ኢንስቲቱት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ፣ የእርሻ ምርትንና ምግብን የሚያጠቃልልና የነፃ ንግድን በአባል አገሮች መሀከል ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ስር እየሰደደ የመጣው ዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ ቀውስና የብዙ ኢንዱስትሪ አገሮች መንግስታት በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች(Multinational Firms) ቁጥጥር ስር መውደቅና

የነሱን ጥቅም ማስከብር አስፈላጊነቱ እየጎላ ሲመጣ ነው። ተጨባጭ ሁኔታዎች እን ደሚያረጋግጡት ፣ በተለይም የኢንዱስትሪ አገሮች መንግስታት ቀስ በቀስ ከአጠቃላይ የመን ግስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ መላቀቅና የትላልቅ ኢንዱስትሪዎችንና የባንክን መስክ የበለጠ ትርፋማና ሀብት አካባች ለማድረግ እንዲሁም ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥና ከሌላው ተሽሎ ለመገኘት መከተል ከጀመሩት የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም መሰረት ፣ ወደ ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ የዓለም አቀፍ ኩባን ያዎች ግፊትና ተሰሚነት እየጎላ በመምጣት መንግስታቱን መፈናፈኛ አሳጥቷቸዋል ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታ በዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅቱ ላይ በማንፀባረቅ ፣ በተለይም ጥቂት የእርሻ ምርትንና ምግብን የሚቆጣጠሩ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የንግድ ድርጅቱን በቁጥጥራቸው ስር እያዋሉ መጥተዋል። በዚህ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የወደፊት ሩጫና የበላይነትን መቀዳጀት ድል የተነሳ በንግድ ድርጅቱ አባል አገሮችና ወደፊትም አባል ለመሆን በሚሹ አገሮች መሀከል የውጭ ንግድን ለመቆጣጠር የተጣሉ እገዳዎችን(Protectionist Measures) ሙሉ በሙሉ ማንሳት እንደሚያስፈልግ ስምምነት ተደረሰበት። ማንኛውም አገር የየራሱን ህገ-መንግስትና ሌሎች ህጎችን በመርገጥና የህዝቡን የወደፊት ዕድል በማጨለም የዓለም ንግድ ድርጅቱንና የዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን ድንጋጌ ሳያወላውል በተግባር መመንዘር አለበት። ይህንን በሚመለከት በተዘጋ ቤት ውስጥ የዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅቱና የዓለምን ምግብና የእርሻ ምርት ውጤት የሚቆጣጠሩ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች መሀከል 170 የሚሆኑ አከራካሪ ነጥቦችና ህጎች ላይ ውይይት ተደርጓል። በዚህም መሰረት ማንኛውም አባል አገር የዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት ስምምነትን የሚጥስ እርምጃ ከወሰደ ከፍተኛ ቅጣት ይደርስበታል። ኢትዮጵያም አባል ከሆነች የዚህ ዐይነቱ እርምጃ ፅዋ ቀማሽ ትሆናለች። አይ አልቀበልም ለቅቄ ወጣለሁ ብትል ደግሞ የሚመጣውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግፊት በፍጹም ልትቋቋም አትችልም።

ይህ ዐይነቱ ስምምነት ከመደረሱና ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ፣ በኢንዱስትሪ መስክ በተደረገው ስምምነት ወዝ አደሮችና ተጠሪዎቻቸው ከፍተኛ ግፊት ተደርጎባቸዋል። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የስራ መስኮች ወድመዋል። የብዙ ሚሊዮን ወዝ አደሮች ተጨባጭ ደሞዝ በብዙ እጅ ቀንሷል። አነስተኛ ደሞዝንና አመቺ የማምረቻ ሁኔታዎችን ተገን በማድረግ ከኢንዱስትሪ አገሮች እየተነቀሉ ወደ አንዳንድ የባሪያ ደሞዝ የሚከፈልባቸው የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚተከሉት ኢንዱስትሪዎች በኢንዱስትሪ አገሮች የስራ አጥ ቁጥሩ እን ዲጨምር ከማድረግ አልፎ የሰራተኛው የመግዛት ኃይል እየተዳከመና የመንግስታቱን ባጀት እያዛባው መጥቷል። በሌላ ወገን ደግሞ በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ቁጥጥር ስር ያሉትና በሶስተኛው ዓለም አገሮች የተተከሉት ኢንዱስትሪዎች ለየአገሮች ዕውነተኛ ዕድገት አለማምጣታቸው ብቻ ሳይሆን ፣ በኢንዱስትሪዎቹ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት ወዝ አደሮች ደሞዝ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ የመግዛት ኃይላቸውን ከፍ አላደረገውም። ደሞዛቸውም ለቤተሰቦቻቸው ስለማይበቃ ልጆቻቸውን ለማስተማርና ቁም ነገር ለማድረስ አልቻሉም። ለባርነት የተፈጠሩ ይመስል በዓለም ገበያ ላይ በስራ ክፍፍልና በነፃ ንግድ ስም በሚሽከረከረው ሽፋን ስር ተፈጥሮአዊ ነፃነታቸውን ተገፈው ለዘንተ-ዓለም እንዲቀሩ ተገደዋል። ይህ ነው በየአገሮች አፍጦ አግጦ የሚታየው ሀቅና የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ካልሆን ታንቀን እንሞታልን ብለው አምረረው ለተነሱት መሪዎቻችንና የኢኮኖሚ አማካሪዎቻቸው የማይታያቸው። ይህ ከላይ የተዘረዘረው ጉዳይ የኢንዱስትሪ መስኩን የሚመለከት ሲሆን ፣ በእርሻው መስክ የሚታየው ቀውስና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ገበሬዎችን መብት የገፈፈው ይህ ዐይነቱ በንግድ ድርጅቱና በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች መሀከል ያለው የተቀደሰ ጋብቻ ከፍተኛ መዘዝ አስከትሏል። ከትውልድ ትውልድ ሌሊትና ቀን እየሰሩ በመሰረቱ ትርፍ ለማግኘት ሳይሆን ሙያቸውን እንደ ባህል ያደረጉና ተፈጥሮን እየተንከባከቡ ጤናማ የእርሻ ምርት ለተጠቃሚው ህዝብ የሚያቀርቡ ትናንሽ ገበሬዎች የእርሻ መስኮቻቸውን እንዲዘጉና መንደሮቻቸውን እንዲለቁ ተገደዋል። በአዲሱ የንግድ ስምምነት መሰረት በብዙ የኢንዱስትሪ አገሮችም ውስጥ ህብረተሰብአዊ መዛበት ሊከሰት ችሏል። ይህ ብቻ ሳይሆን የቀሩት ገበሬዎች በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ቁጥጥር ስር በመውደቅ ሶስት የዓለምን የዘር ባንክ በሚቆጣጠሩ ኩባንያዎች ስር ፍዳቸውን እያዩ ነው። በሌላ አነጋገር ማን

ኛውም ገበሬ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በሙከራና በልምድ ያዳቀለውን የእህል ዘር የመዝራት ዕደል የለውም። ከብድር ጀምሮ እስከ ዘርና የኬሚካል ማዳበሪያዎች እንዲሁም የተባይ ማጥፊያ ድረስ በባንክና በኩባንያዎች ቁጥጥር ስር የወደቀ በመሆኑ ፣ ገበሬዎች በቀጥታ የሚሰሩት የኩባንያዎችንና የባንኮችን ሀብት ለማካበት ነው። ገበሬዎች ሀብት አፍርተው የረጋና የተደላደለ ኑሮ መኖር አይችሉም ማለት ነው። የነፃ ገበያ ውድድርና ይህ ዓይነቱ ጥገኝነት ብዙ ሰዓት መስራትንና ራስን ከሚገባው በላይ ማሰጨነቅ ይጠይቃልና።

ይሁንና ይህ ዐይነቱ ነፃ ንግድን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ስምምነት ቢደረስም በአንድ በኩል በአሜሪካና በብዛት የእርሻ ምርትን ለዓለም ገበያ በሚያቀርቡት የኬይርነስ ተወካዮች(Cairns-Groups) ማለትም ፣ አርጀንቲና ፣ አውስትራሊያ ፣ ካናዳ ፣ ብራዚል ፣ ኒው-ዘላንድ ፣ ኡራጓዋይ ፣ ቺሌ ፣ ኮሎምቢያ ፣ ፓራጉዋይ ፣ ማሌዢያ ፣ ኢንዶኔዢያ ፣ ደቡብ አፍሪቃ ፣ ታይላንድና ፍሊፒን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በአውሮፓ የጋራ ገበያ አገሮች መሀከል የጦፈ ክርክር ይካሄዳል። የውጭውን ንግድ ሙሉ በሙሉ ነፃ ማድረግ ፣ ወደ ውስጥና ወደ ውጭ የሚደረገውን ድጎማ ሙሉ በሙሉ መሰረዝ ፣ ቀጥተኛና በንዑስ መስኮች መሀከል የሚደረገውን ክፍያና ማስተካከያ ማቆም የሚሉት ናቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ የአውሮፓው የጋራ ገበያ አሻፈረኝ ሲል ፣ አሜሪካ በጥንቃቄ "እየተቀበለው" መጥቷል። ስምምነቱ ከተደረሰ ጀምሮ በተለይም እንደነ ብራዚል ያሉት የስኳርን ምርት በዓለም ገበያ ላይ በማራገፍ የተሻለ ዕድል ቢያጋጥማቸውም እንደነ ኡራጓይ ያሉት አገሮች ደግሞ አባል ሆነውም በስምምነቱ መሰረት የተሻለ የገበያ ዕድልና ወደ ውስጥ ደግሞ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕደገትንና የሀብት ክምችትን ሊያዳብሩና ህዝቦቻቸውን ከደህነት ሊያላቅቁ በፍጹም አልቻሉም። በአንጻሩ በተለያዩ ዘዴዎች የእርሻ ምርቶቻቸውን ወደ ኢንዱስትሪ አገሮች የመላክ ፣ በተለይም የአውሮፓ የጋራ ገበያ አገሮች ውስጥ የማስገባቱ ዕድል እየጠበበ መጥቷል። በሌላ አነጋገር እ.አ.አ በ1994 ዓ.ም የእርሻ ምርትንና ምግብን በአለም አቀፍ ገበያ ላይ እንደተፈለገው ለማራገፍ የተደረሰበት ስምምነት ይበልጥ የጠቀመው የአውሮፓ የጋራ አገሮችንና አሜሪካንን ሲሆን ከታዳጊ አገሮች ውስጥ ደግሞ ብራዚልን ብቻ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ብራዚል ውስጥ አርባ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ የምግብ እጥረት አለበት። በስኳር ምርት የተነሳና መሬት በጥቂት ኦሊጋርኪዎች በመያዙ ህዝቡን በምግብ ለማዳረስ ያለው ችግር ከፍተኛ ነው። ፕሬዚደንት ሉላ ከዚህ ሀቅ በመነሳት ነው ከተመረጡ በኋላ እያንዳንዱ ብራዚሊያዊ ቢያንስ በቀን ሶስት ገዜ በልቶ እንዲያድር አደርጋለሁ ብለው ቃል ኪዳን የገቡት። ይህ ቃል ኪዳናቸው የቱን ያህል ተግባራዊ መሆኑን አለመሆኑን የሚያረጋገጥ ማስረጃ የለም።

ከላይ በተጠቀሱት አገሮችና በአውሮፓ የጋራ ገበያ መሀከል የሚደረገው ክርክር እራሱን የነፃ ገበያን አራምዳለሁ የሚለውን የአውሮፓ የጋራ ገበያ ቅራኔ ውስጥ እየከተተው መጥቷል። የአውሮፓው የጋራ ገበያ በየዓመቱ ለገበሪዎቹ 99 ሚሊያርድ $ ድጎማ ይሰጣል። የኢንዱስትሪ አገሮች በአጠቃላይ 311 ሚሊያርድ $ ድጎማ ለገበሬዎቻቸው ይሰጣሉ። ይህንን ድጎማ ሙሉ በሙሉ ማንሳት የገበሬውን መስክ እንዳለ ያፈራረሰዋል። ይህ አንደኛው የአውሮፓ የጋራ ገበያ የገባበት ጥምጥም ሲሆን ፣ ሌላ የሚሰጠው ምክንያት ደግሞ የገበሬውን መስክ ሰፋ ያለ ተግባርና በህብረተሰቡ ላይ ያለው ባህላዊ ተፅዕኖ አነስም በዛም ከፍተኛ በመሆኑ ይህንን ዘርፍ ማዳከም እንደሰንስለት የተያያዘውን ኢኮኖሚያዊ ክንውን በከፍተኛ ደረጃ እንደማናጋት ይቆጠራል የሚል ነው። ይህ ጉዳይ በአንድ በኩል በምርት ብዛት የተወጠረውን የአውሮፓ የጋራ ገበያ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ እንደፈለገው በሶስተኛው ዓለም አገሮች ምርቱን ለማራገፍ የሚያደርገውን ሩጫ ለማመቻቸት ያለውን ቀዳዳ ለመጠቀም ያለመቻል ጉዳይ ቅራኔ ውስጥ ከትቶታል። ይህ ጭንቀት 10 አዲስ አባል አገሮች የአውሮፓን የጋራ ገበያ ከተቀላቀሉ በኋላ ልዩ መልክ እየያዘ መጥቷል። አዲሶቹ አባል አገሮች ገበያቸውን ክፍት ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን እነሱም የብስኩቱ ተካፋይ እንደመሆናቸው መጠን የእርሻ ምርቶቻቸውን ወደ ሌሎች የመጀመሪያዎቹ አባል አገሮች መላክ አለባቸው። ሌላ አዲስ የታቀደ ቅራኔ መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ፣ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የተዝረከረከ የእርሻ ምርት መስክ ያላቸውና የዓለም ንግድ ድርጅት እንግባ እንግባ እያሉ የሚፍጨረጨሩ ፣ የአውሮፓ የጋራ ገበያ ፣ የአሜሪካና የሌሎች የድርጅቱ አባል አገሮች ገበያ ላይ ምርታቸውን ለመሸጥ ያላቸው ዕድል በጣም የጠበበ ነው። እነዚህ አገሮች በሰበብ ባሰባቡ ገበያቸውን ማጥበባቸው

የማይቀር ጉዳይ ነው። ከነዚህ ውስጥ የጥራት ጉዳይና ከምርቶች ጋር ተያይዘው ይመጣሉ ተብለው የሚገመቱ በሽታዎች እንደምክንያት ሊቀርቡ ይችላሉ። በዚህ ላይ በተለይም የአውሮፓው አንድነት ገበያውን ለመዝጋት ሲል ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል። በሌላ ወገን ግን ወደ ፊት እየሰፋ የሚመጣው የንግድ ልውውጥ ፣ ማለትም የአገልግሎት የጤና መስኩን ልቅ ማድረግ ፣የውሀና የትምህርት መስኩን በሚመለከት ለዓለም አቀፍ ተዋናዮች ክፍት ማድረግ ፣ ወዘተ... ወዘተ... እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን በንግድ ድርጅቱም ሆነ በአውሮፓ የጋራ ገበያ ታምኖበታል። በየአገሩ ገብተን እንደፈለግን እንፈትፍት የሚለው ዐይን ያወጣ ውትወታ በኢኮኖሚያቸው ደካማ የሆኑ አገሮችን በጣም አሰጨንቆአቸዋል። ወደፊት አምባ ገነን ዓለም አቀፋዊ መንግስት ሊመሰረት ነው የሚል ፍርሀቻ በብዙዎች ዘንድ ሰፍኗል። ወደፊት ገበያው ሁሉንም መስክ የሚያጠቃልል በመሆኑ የብዙ አገሮች ብሄራዊ-ነፃነት መደፈሩ የማይቀር ነው።

ይህ በአውሮፓ የጋራ ገበያ ወይም በአሁኑ ወቅት የአውሮፓ አንድነት እየተባለ የሚጠራው እንደዚህ ባለቅራኔ ውስጥ ተውጥሮ እያለ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የአፍሪቃን ፣ የካሪቢክና የፓሲፊክ አገሮችን ፣ ማለትም የሰባሰባት አገሮችን ቅንጅት የንግድና የዕድገት ፈለግ በአዲስ መልክ ለማደራጀትና ይበልጥ በኢኮኖሚያቸው ውስጥ ጣልቃ ለመግባት የማያመቻቸው ነገር የለም። በዚህም ምክንያት የአውሮፓው አንድነት ከእነዚህ አካፔ(AKP) አገሮች ጋር የኢኮኖሚ ግኑኝነት ስምምነት በሚል ሽፋን ስር ከዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅቱ ደንቦች ጋር በሚጣጣም መልክ ጠለቅ ያለ ውይይት እያደረገ ነው። በአውሮፓው አንድነትና በእነዚህ 77 አገሮች መሀከል ለመጀመሪያ ጊዜ እ.አ.አ በ1975 ሎሜ ላይ ፣የሎሜ ስምምነት ተብሎ በሚጠራ ስምምነት ይደረሳል። በዚህም ስምምነት መሰረት እነዚህ 77 አገሮች በአውሮፓው አንድነት ገበያ ውስጥ ዕቃቸውን ሊያራግፉ የሚችሉበት ሁኔታ "ይመቻችላቸዋል"። እ.አ በ2000 ዓ.ም ኮንቱን በሚባል የቤኒን ዋና ከተማ 77ቱ አገሮችና የአውሮፓው አንድነት አዲስ የንግድ ግኑኝነት ስምምነት ይፈራረማሉ። በዚህ ኮንቱን ላይ በተደረሰው ስምምነት መሰረት ሰባሰባቱ አገሮች ከዓለም የንግድ ድርጅት ህግ ጋር የሚስማማ የንግድ ውል መቀበል አለባቸው። ከውጭ ወደ ውስጥ የሚገቡ ንግድን የሚያደናቅፉ ማን ኛውም ደንቦች ቀስ በቀስ እንዲሉ መወገድ አለባቸው።ውይይቱ እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ መጠናቀቀ ሲኖርበት ፣ ከ2008 እስከ 2020 ዓ.ም ድረስ ስምምነቱ ተግባራዊ ይሆናል።ይህ የአውሮፓው አንድነት ከእነዚህ የአካፔ አገሮች ጋር የሚያደርገው ድርድር ልዩና ከዚህ ቀደም ወደ አንድ አቅጣጫ ያዘነበለ ፣ በሌላ አነጋገር የ77 አገሮችን ጥቅም የሚያስቀድመውን ውል በማስፋፋት የአውሮፓው አንድነት የበለጠ ጥቅም የሚያገኝበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው። በዚህም መሰረት የአውሮፓ አንድነት በእነዚህ ስምምነት በደረሰባቸው አገሮች ውስጥ ሰርጎ በመግባት ገበያቸውን የመቆጣጠርና የየአገሮችን አምራች ኃይል ሊያዳክም እንደሚችል ቀደም ብለው የወጡ ጥናቶች ያመለክታሉ። እራሱ በአውሮፓ ኮሚሽን የተጠናቀረው ጥናት እን ደሚያረጋግጠው ስምምነቱ ከተደረሰና ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ እነዚህ 77 አገሮች ከአውሮፓው ምርት ጋር በፍጹም ለመወዳደር እንዳማይችሉና የኢኮኖሚያቸውን መከስከስ እን ደሚያፋጥነው ነው። 77 አገሮች የአውሮፓ ጋራ ገበያ ውስጥ ገብተው ለመወዳደር የውስጥ ገበያቻውን በማዳከምና ሌሎች ለማህበራዊ ድጎማና መዋዕለ-ነዋይ የሚያውሉትን ወጪ ወደ ውጭው ኢኮኖሚ ላይ በማሸጋሸግ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ድክመትንና ህብረተሰብአዊ መዘበራረቅን እንደሚያስከትልባችው ይህ ጥናት ያመለክታል።እንግዲህ ይህ ሁኔታ እያለ የአገራችን መሪዎችና አማካሪዎቻቸው ይህንን ጥድፊያ ለምን ተያያዙት? ነገሩ እንቆቅልሽ ነው የሚመስለው።

ይህ ጉዳይ በእንደዚህ እያለ በተለይም እ.አ.አ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ የእርሻ ምርት ዋጋ በዓለም ገበያ ላይ እየቀነሰ እንደመጣና በተለይም ብዙ አፍሪቃ አገሮች የውጭ ምንዛሪያቸው በጣም ዘቅ እያለ በመምጣቱ ዕዳ ውስጥ እንደገቡ ስታትስቲክሶች ያመለክታሉ። በአጠቃላይ የእርሻ ምርት ዋጋ በአለፉት ሰላሳ ዐመታት በዓለም ገበያ ላይ 40% ያሀል ዝቅ ብሏል። ይህ ሁኔታ እየባሰ የሚሄድ እንጂ የሚሻሻል አለመሆኑን ብዙ ጥናቶች ያመለክታሉ። በውቅር የማስተካከያ ስምምነት(Structural Adjustment Program) አማካይነት የተደረገው የገንዘብ ቅነሳ ፖሊሲ(Currency davaluation) እንደተጠበቀው በዓለም ገበያ ላይ ምርታቸውን በብዛት እን

ዲያራግፉ አመቺ ሁኔታ አልፈጠረላቸውም። እንዲያውም ይባስ ብሎ ገቢያቸው እየቀነሰ መጥቷል። ከዚህ ጋር ባለፈው ሰላሳ ዐመት የተካሄደው የቴክኖሎጂ ምጥቀት ፣ በተለይም በባዮ ቴክኖሎጂ የተፈጠሩት አዳዲስ ምርቶችና ሲንቴቲክ ውጤቶች ከሶስተኛው ዓለም የሚመጡ የእርሻ ምርቶችን ለመወዳደር በቅተዋል። በሌላ አነጋገር አንድ በእርሻ የምትመካ አገር በዓለም ገበያ ላይ ተወዳድራ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን የመጎናፀፍ ዕድሏ በጣም የመነመነ ነው ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ፣ ለአርባ ዐመት ያህል የኮታን ገደብ ያቀፈው አንቀጽ በቅርቡ ስለሚነሳ-ጊዜው ስለአለቀ- ከእንግዲህ ወዲህ በኮታ አሳቦ የአገርን ገበያ መከላከል በፍጹም አይቻልም። ይህ በተለይም የጨርቃ ጨርቅ ምርትን የሚመለከት ሲሆን ፣ በዚህ የኮታ ገደብ መነሳት ቻይና እንደምትጠቀም ከአሁኑ ግልጽ ነው። ጉዳዩ ብዙ የአውሮፖ አገሮቸን አስፈራርቷል።እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮችም የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካቸውን እን ዲዘጉ ይገደዳሉ።

ከዚህ አነሳም በዛም ከተብራራው መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የአገራችንን የኢኮኖሚ ሁኔታና በዓለም ላይ ልታቀርብ የምትችለውንና እስካሁን ድረስ በተወሰኑ የእርሻ ምርት ላይ ማትኮሩ የቱን ያህል የኢኮኖሚውን ዕድገት እንዳገዛውና እንዳላገዘው አጠር ባለ መልክ እንመልከት።

## <u>የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታ የንግድ ድርጅቱ አባል ለመሆን ያመቻል ወይ ?</u>

አንድ አገር የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ቅንጅት አባል ከመሆኗ በፊት ፣ 1ኛ) አገዛዙ የአገሩን የኢኮኖሚ አወቃቀርና ለዕድገት ማነቆ የሆኑትን ምክንያቶች በሚገባ መገምገም አለበት። 2ኛ) የዓለምን ኢኮኖሚያዊ አወቃቀርና የኃይል ሚዛን አሰላለፍ ማጥናት አለበት። 3ኛ) ይህ በምን የኢኮኖሚ ሎጂክና ርዕዮተ-ዓለም እንደሚመራ ሰፊ ጥናት ማካሄድ አለበት። 4ኛ) እስከዛሬ ከተደረጉት ስምምነቶች ሌሎች አገሮች የቀሰሙትን ልምድና ያገኙትን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። 5ኛ) እንደ ኢትዮጵያ ያለች የተዘበራረቀ ኢኮኖሚ ያላት አገር የዚህ ዐይነት ድርጅት አባል ብትሆን ምን ጥቅም ታገኛለች ብሎ ሰፋ ያለ የቲዎሪ ፣የሳይንስና ተጨባጭ ጥናቶችን ማካሄድ ያስፈልጋል። በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ ኢኮኖሚያዊ ክንውንና ዕድገት ልትቀዳጅ ትችላለች ወይ ? ሰፋፊና የሚያምሩ ከተማዎችን ፣ የባቡር ሀዲዶችን ገንብታ ጥቅላላው ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ወይ? ብሎ መንግስቱ በአሉት ኢንስቲቱሽኖች አማካይነት መገምገምና ጥቅሙንና ጉዳቱን ማመዛዘን ይኖርበታል። ከዚህ በላይ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶች ያላቸውና ጥቅም የሚያገኙና የሚጎዱ እንደመኖራቸው መጠን ከህብረተሰብ ውስጥ የሚቀርቡትን ጥናቶችና ቅሬታዎች እንዲሁም ትችቶች ጠጋ ብሎ መመርመርና በራስ ጥናት ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል። ይህንን ሳያደርጉ ከውጭ ኤክስፐርት ነን ከሚሉ ጋር በዚህም በዚያም ብሎ ተመሰጣጥሮ ወደ ስምምነት መድረስና ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር የብዙ ትውልድ ዕድል እንዲጨልምና ታሪክ እንዲበላሽ ያደርጋል። ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የቱን ያህል ተወዳዳሪ መሆኑንና አለመሆኑን ለመረዳት አወቃቀሩን ገርደፍ ገርደፍ እያደርግን እንመልከት።

ሁኔታውን ለመገንዘብ ኢኮኖሚውን በሶስት መስክ ከፋፍለን እንመልከተው። 1ኛ) የእርሻው መስክ ፣ 2ኛ) የኢንዱስትሪው መስክ ፣ 3ኛ) የአገልግሎቱ መስክ ናቸው።

በመጀመሪያ የእርሻውን መስክ እንመልከት። ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው የእርሻ ተግባር ከእጅ ወደ አፍ (Subsistence Economy) የማያልፍ ክንውን መሆኑን ለማንኛውም ሰው ግልጽ ነው። የገበሬው ውስጣዊ አደረጃጀትና ያወጣውን ዋጋ በማስላት ትርፍ ለማካበትና ገሚሱን ደግሞ እንደገና ኢንቬስት በማድረግ ለመወዳደር የሚያስችለው ሳይሆን በዘልማድ ተደግፎ የሚንቀሳቀስ ነው። በሌላ አነጋገር በካፒታሊስት ሎጂክ የሚመራ አይደለም ማለት ነው። ይሁንና አብዛኛው ገበሬ እንደምንም ተፍጨርጭሮ ከራሱ አልፎ ጠቅላላውን ህብረተሰብ የሚመግብ ነው። የሚያገኘው ገቢ ቀላል የፍጆታ ዕቃዎችንና እራሱ የማያመርተውን ጨውና

ለምባ ከመግዛት አልፎ የሚሄድ አይደለም። ገበሬው የህብረተሰቡ የምግብ መሰረት መሆኑ እየታወቀና ህብረተሰቡን ለመመገብ ግዴታ ያለበት ይመስል ከመንግስት የሚሰጠው ድጋፍ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። እንዲያውም በታቃራኒው በመንግስት በደል ይደርስበታል። የመንግስቱ ኢንስቲቱሽኖች በከተማ ውስጥ ብቻ የሚንቀሳቀሱ እንደመሆናቸው መጠን-ለምሳሌ የእርሻ ሚኒስቴር- ከገበሬው ጋር ምንም ዐይነት ግኑኝነት የላቸውም። በዚህም ምክንያት ገበሬው ለብዙ ዐመታት እራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ነው ማለት ይቻላል።

በተደጋጋሚ በአገራችን የተከሰተው ረሀብ ገበሬውን ከውጭ በዕርዳታ መልክ በሚመጡ እህሎች እንዲጠቃ አድርጎታል። የተወሰነው ከውጭ የሚመጣው ስንዴና በቆሎ ገበያ ውስጥ በመፍሰሱ ከገበሬው ምርት ጋር በመወዳደር የገበሬውን ገቢ የማግኘትና የመግዛት ኃይል እንዲመታ አድርጓል። በዚህ ውድድር ተሰፋ የቆረጠው የተወሰነው ክፍል ወደ ሌላ ምግብ-ነክ ወዳልሆኑ አትክልቶች ሲሰማራ ፣ ሌላው አምራች ደግሞ ሰብሉን ወደ ገበያ አምጥቶ የሚገዛው ሲያጣ ለመመለስ ስለሚቸገር እየደፋው ወደ መጣበት ይመለሳል። ከዚህም በላይ መንግስት ካለምንም ጥናት ገበሬውን እያስገደደ ማዳበሪያና ዘር ግዛ እያለ ብድር በመስጠት አብዛኛው ገበሬ መክፈል ባለመቻሉ ማሳውን እየለቀቀ ወደ ከተማዎች እን ዲሰደድና ወደ አልባሌ ስራ እንዲሰማራ ተገዷል። በሌላ አነጋገር ከአስራ አራት ዐመት ጀምሮ በአገራችን ምድር ተግባራዊ የሆነው ነፃ ገበያ ገበሬውን በከፍተኛ ደረጃ መትቶታል። በዚህ ምክንያትና የአገሪቱ ገበያ ያልዳበረ በመሆኑ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት አባል ብትሆን በተለይም ገበሬው የባሰውኑ ይጎዳል። ገበሬው ወደ ከታማዎች እየፈለሰ በመምጣት የስራ-አጥ ቁጥሩን እንዲጨምር ያደርጋል። በዚያው መጠንም ለአንድ ህብረተሰብ አስፈላጊ የሆነው የገጠር የእርሻ ክንውንና ባህል እየተዳከመ ይመጣል። የታቀደ ህብረተሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ መዘበራረቅ ይፈጠራል።

ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸውን የእርሻና የከብት ውጤቶች ደግሞ እንመልከት። አገራችን ከሀምሳ ዓመታት በላይ የውጭ ምንዛሬ ለመቃረም በጥቂት የእርሻ ሰብሎች ላይ ነው ስትመካ የኖረችው። ከዚህ ውስጥ ቡና ከፍተኛውን ቦታ ሲይዝ ፣ ይህ ተፈልፍሎ ፣ ታጥቦና ደርቆ ወደ ውጭ በጥሬ መልኩ የሚላክ እንጂ ተፈጭቶና ታሽጎ አይደለም። በመሆኑም የቡና ተከላና ምርት ወደ ውስጥ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያለው ትርጉም እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። አይደለምም። በዚህም ምክንያትና በአለፈው አሰር ዐመታት አዳዲስ የቡና አምራች አገሮች በዓለም ገበያ ላይ ብቅ በማለታቸው ኢትዮጵያ ከቡና ሽያጭ የምታገኘው ገቢ ከዐመት ወደ ዐመት እየቀነሰ መጥቷል። ይሁንና ይህ አፍጦ አግጦ ያለ ሀቅ እያለ መንግስትም ሆነ በቡና ምርት የተሰማሩ ገበሬዎችና ነጋዴዎች ቡናን የኢኮኖሚው ዋናው አንቀሳቃሽ ኃይል አድረገው ይመለከቱታል። ገፋተው በመሄድም አንዳንድ የኢንዱስትሪ አገር መሪዎች በዓለም የቡና ገበያ ላይ ዋጋው ከፍ እንዲል ተፅዕኖ እንዲያደርጉ ይማፀናሉ። የቡናን ዋጋ እነሱ ይቆጣጠሩ ይመስል። ይህ እርምጃቸው የዋህነትን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ካፒታሊዝም በምን ዐይነት ሎጂክ እንደሚንቀሳቀስ ለመረዳት ያለመቻልን የሚያሳይ ነው። ሌሎች የከብት ውጤቶች ከኢኮኖሚ ዕደገት አንፃር ጥቅማቸው ይሀን ያህልም ጉልህ ሳላይደለ ማተቱ አሰፈላጊ አይደለም። በአጠቃላይ የግሎባል ካፒታሊስት ኢኮኖሚ የኛን አገር እንደዚህ ክፉኛ እየተፈታተነን ባለበት ወቅት አሁን ደግሞ የተያዘው ለምለም የሆነውን መሬት አበባ እንዲተክልበት ማድረግና ወደ ውጭ በመላክ የአገሪቱን ኢኮኖሚ የባሰውን ማዘበራረቅ ነው። ይህም ደግሞ ሁለትና ሶስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ለመቃረም ሲባል ነው። ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ዕብደት በአገራችን ምድር ተከስቷል ማለት ነው። የፖለቲካ ኢኮኖሚክስን ሀሁ የተገነዘበ አበባ ወደ ሌላ ምርት የሚለወጥ ሰብል አይደለም። በሌላ አነጋገር በኢንዱስትሪ ውስጥ ገብቶ ወደ ሌላ ምርትነት(Value Added) የማይለወጥ ኢኮኖሚያዊ ትርጉም ሊኖረው በፍጹም አይችልም። በአሁኑ ወቅት ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ወደ አበባ ምርት ላይ ስለተሰማሩ ፣ ይህም አንድ ቀን ገበያው እየጠበበ ይመጣል። ከዚያም የሚገኘው ገቢ እንደዚሁ እየቀነሰ ይመጣል። ከዚህ ስንነሳ ኢትዮጵያ አሁን ባላት ኢኮኖሚያዊ ቅንጅት በፍጹም በዓለም ገበያ ላይ ለመወዳደር የሚያስችላት የእርሻ መስክና ሰብል የላትም ማለት ነው።

የኢንዱስትሪውን መስክ ደግሞ እንመልከት። የአገራችን የኢንዱስትሪ አወቃቀር ስትራቴጂክ በሆኑና እየተባዙ በሚሄዱና ለሌላው መሰረት በሚሆኑ ላይ የተመረኮዘ የምርት ክንውን አይደለም። ኢንዱስትሪዎቹ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የተደገፉ ሳይሆኑ ለመለዋወጫና በግማሽ ለተፈበረኩ ምርቶች በወጭ ገበያ ላይ ጥገኛ ናቸው። ውስጣዊ ኃይላቸው እጅግ ደካማ ነው። ከዛሬ አስራ አራት ዐመት ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው ነፃ ገበያና የውጭውን መስክ ከቻይናና ከሌሎች ኢንዱስትሪ አገሮች ለሚመጡ ዕቃዎች ልቅ በመደረጉ የኢን ዱስትሪውን መስክ ክፉኛ እንደመታው ግልጽ ነው። በተለይም ትናንሽ አምራቾች ከቻይናና ከደቡብ ኮሪያ በሚመጡ ምርቶች በመመታታቸው ገበያውን እየለቀቁ እንዲወጡ በመገደድ የድህነትን ፅዋ እንዲቀምሱ ተገደዋል። በመሆኑም አገራችን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ብትሆን ያሉት ኢንዱስትሪዎች መመታታቸው ብቻ ሳይሆን ጠቅላላው የወስጥ ገበያ ወደ መፈረካከስ ያመራል። ስራ-ፈት መብዛትና የመግዛት ኃይል መዳከም የአገሪቱ መለዮዎች ይሆናሉ።

የአገልግሎት መስኩን እንመልከት። ይህ መስክ ሰፊና በጣም የተዝረከረከ ነው። ይህን ያህልም ከኢንዱስትሪው ጋር የተያያዘ አይደለም። ስለዚህም በተወሰኑ ዘርፎች ላይ እናተኩር። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ነፃ ገበያን ተገዳ እንድትቀበል ከተደረገች ወዲህ ዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መንግስቱን የሚነዘንዙት ፣ የመብራት ኃይል ፣ ስልክን ፣ የውሀውን ፣ የጤንነትና የትምህርት መስኩንና የባንኩን መስክ ልቅ አድርግ ፣ መጥተን እንዳሻን እንረባረብበት እያሉ ነው። የአገራችን ከበርቴ ደግሞ በዚህ መስክ ለመሰማራት ገንዘብም ሆነ የአደረጃጀትና የዕውቀት መሰረት የለውም። ያም ሆነ ይህ መስክ ለውጭ ከበርቴዎች ቢሸጥ የመስፋፋትና ለህዝቡ አገልግሎት የማዳረስ ኃይል በፍጹም አይኖረውም። ማንኛውም ከውጭ የሚመጣ ገበርቴ ቴክኖሎጂ ይዞ በመምጣት ኬብሎች በማስፋፋት ፣ የስልኩን ቴክኖሎጂ በማሻሻልና የሰው ኃይልም ለማሰልጠን ሳይሆን የተወሰነውን ክፍል በመዝጋትና ሰራተኛን በማባረር ትርፍ ለማካበት ነው። ወይም ደግሞ የሞባይል ስልክ በማስፋፋት ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ባለቤት እንዳትሆን ማድረግ ነው። የብዙ ሶስተኛው ዓለም አገሮች ልምድም ይህንን ነው የሚያረጋግጠው። የውሀም መስክ ይህን ዐይነቱ ዕጣ ሲደርሰው አብዛኛው ህዝብ ንጹህ ውሀ የመጠጣት ዕድሉ እየመነመነ ይመጣል። የፊሊፒን ሁኔታ ይህንን ያረጋግጣል። የውሀው መስክ በፈረንሳይና በአሜሪካ ኩባንያዎች በመያዙ አብዛኛው ህዝብ ቆሻሻ ውሀ እንዲጠጣ ተገዷል። ከዚህ ስንነሳ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ብትሆን ይህንን መስክ ለውጭ ከበርቴዎች ክፍት የማድረግ ግዴታ ስላለባት በቀጥታ ህዝባችን ይበደላል። ይህ መስክ ሊዳብር የሚችለው ወደ ውስጥ የቴክኖሎጂ አብዮት ሲካሄድና በብዛት የሰው ኃይል ሲሰለጥን ብቻ ነው። በዓለም ታሪክ ውስጥ አንድ አገር ገበያዋን ለውጭ ከበርቴዎች ልቅ አድርጋ ያደገችበትና የቴክኖሎጂ ምጥቀት ያየችበት ጊዜ ታይቶ በፍጹም አይታወቅም።

ይህ አንደኛውና ያገራችንን ኋላ ቀርነት የሚያራዝመውና የሚያባብሰው አደገኛ እርምጃ ሲሆን ፣ በአዲሱ ዓለም አቀፋዊ የብድር አሰጣጥ ስምምነት መሰረትን በፊናንስ ኦሊጋርኪ የተጫነው ትናንሽና ማዕከለኛ አምራች ከበርቴዎችን የመምታት ስትራቴጂ የገንዘብ ፖሊሲ ወደ ፊት በንግድ ድርጅቱ ደንብ ውስጥ ይጠቃለላል። በዚህ ባዝል ሁለት(Basel II) ስምምነት ተብሎ በሚጠራው ደንብ መሰረት ባንኮች ብድር መስጠት ያለበቻው ብቃት ላላቸውና እን ደመያዣ በቂ ሀብት ለማሳየት ለሚችሉ ብቻ ነው። ትናንሽ ከበርቴዎች ብድር ከማግኘታቸው በፊት ብዙ ፈተናዎች ማለፍ አለባቸው። ከዚህ ቀደም መንግስታት እንደ ዋስ ሆነው ይጠቀሙበት የነበረውና ትናንሽ ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ ፖሊሲ ከእንግዲህ ወዲህ ተግባራዊ አይሆንም። የማስትሪቹም ስምምንትና አስራ ሁለቱን የጋራ ገበያ አባል መንግስታት አለፈናፍንም ያለው አርቲፊሻል ፖሊሲ የዚህኛው አንደኛው ክፍል ነው። አባል አገር የራሱን የገንዘብና የፊናንስ ፖሊሲ በፈለገው መልክ ለማደረጀትና ረከስ ያለ ብድር ለአምራቹ የህብረተሰብ ክፍል ለማቅረብ በፍጹም አይችልም ማለት ነው። ኢትዮጵያችንም የንግድ ድርጅቱ አባል ብትሆን የራሷን የፊናንስና የገንዘብ ፖሊሲ ከመከተል ትገደባለች። የኢን ዱስትሪ አብዮት ለማድረግ በፍጹም አትችልም።

***ይህንን ሁኔታና የአለፈውን*** 50 ***ዓመታት የተካሄደውን የተዛባ የንግድ ልውውጥ ፣ የዕዳ ክምችትና የግሎባል ካፒታሊዝም ልቅ በሆነ መልክ መስፋፋት አስመልክቶ በአለፈው አስር ዐመታት ከፍተኛ ተቃውሞና እንቅስቃሴ በየቦታው ተካሄዷል። በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካን ከተማዎች የዓለም ንግድንና ኢኮኖሚን አስመልክቶ ጂ ሰባት ወይም ስምንት ፣ ወይም ደግሞ ጂ ሃያ የሚባሉት ሰባት የኢንዱስትሪ አገሮችንና አስራ ሶስት ታዳጊ አገሮችን*** (Newly Industrialized Countries) ***ያቀፈ ስብሰባ በሚካሄበት ቦታ ሁሉ የሚደረገው ተቃውሞ የዕብዶች ሳይሆን ብዙ አወቂዎችንን ያሰባሰበና የሚያገናኝ ለመንግስታቱና ለአፈቀላጤዎቻቸው ራስ ምታት የሆነ ነው። ለአንዳንድ የስልጣኔን ትርጉምና የሰውን ልጅነት ምንነት ላልተረዱ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ነገ ባዮችና ዕድላቸውን ከዓለም ቀኝ ኃይሎች ጋር ለጣመሩ ይህ ሰፊ እንቅስቃሴ የአክራሪዎችና የልጆች ጨዋታ ሆኖ መታየት ከጀመረ ሰንብቷል። ለአገራችንም መሪዎችና አማካሪዎቻቸው ይህ ተቃውሞና እሮሮ እንዲሁም ደግሞ ሰፊ ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደዚሁ እንደቀልድ መታይቱ የማይቀር ነው። በልቶ ፣ ጠግቦና ተደስቶ ለሚኖር የሌለው ብሶትና ድህነት አይሰማውምና። ከዚህ አጭር ሀተታ በመነሳት ኢትዮጵያ በምንም ሁኔታ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን የለባትም። ሀተታዬን ከመደምደሜ በፊት ፣ የዛሬው መሪዎቻችንና አማካሪዎቻቸው እንዲሁም ደግሞ ነፃ ገበያን በተሳሳተ መልክ ለተረዱት የቀኝ ኃይሎች ይህ ሎጂካቸውና ውጣ ውረድ ከተሳሳተ የቲዎሪና ዕውቀት የመነጨ መሆኑን አጠር መጠን ባለ መልክ ለማሳየት እሞክራለሁ።***

## ***<u>የውጭ ገበያ ወይስ የወስጥ ገበያ ነው የአንድ አገር የዕድገት መሰረት?</u>***

***በአጠቃላይ የሰውን ልጅ ዕድገትና ስልጣኔ በሚመለከት ከሶስት ሺህ ዐመት ጀምሮ ክርክርና ምርምር ተካሂዷል። ይህ ክርክር በተለያዩ ጊዜ ብቅ ላሉ ፈላስፋዎችና ተመራማሪዎች እንደህብረተሰብ ዝንባሌያቸው ይህኛውን ወይም ያኛውን ፈለግ በመከተል ህብረተሰብን ያከራከረና አልፋ አልፎ ያጋጨ ነው። በዛሬው ወቅትም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደው ትግልና ክርክር ከዚህ ወጭ አይደለም። ከጥንቱ ይልቅ የዛሬውን ዐይነተኛ የሚያደርገው ፣ የአሁኑ ትግል አምሮ አሽብርቆ መከሰቱ ሲሆን ፣ ይህም ብዙዎችን ወደ ማሳሳት አድርሷል። ሀቀኛውን የስልጣኔ ፈለግ ከተሳሳተው ለመለየትና አንዳች ድምደማ ላይ ለመድረስ አሰቸጋሪ ሆኗል። በአሁኑ ወቅት በአንዳንዶች ለዕውነተኛ ስልጣኔ ለሚታገሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ነፃ ገበያን ለመቃወምና ለመቀበል ያለ ችግር ሳይሆን እንዴት አድርጎ ይህንን በሳይንሳዊ መልክ ለማስረዳት ይቻላል የሚል ነው። ጥያቄው በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ ፣ ግለሰብአዊ ድርጊትንና ፈጠራን የማያፍን ግን ደግሞ መንግስታዊ ቁጥጥር ያለበት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ክንውን ወይስ አገሮችን ለጥቂት ዓለምን ለሚያተራምሱ ተዋናዮችና***(Glbal Players) ***እስከአፍንጫቸው ድረስ በሃይ ቴክ የጦር መሳሪያ ለታጠቁ መን ግስታት አፍ ከፍቶ ፣ በርን በርገግ አድርጎ መስጠት ነው በሚለው ነጥብ ላይ ነው። በእኛ ሀቀኛ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የነፃ ገበያን በተሳሳተ መልክ ለተረዱት የውር ድንብራቸውን በሚመሩትና በተጫበጭ ህብረተሰብን የሚያመሰቃቅል ፖለቲካ በሚከተሉት ቀኝ ኃይሎች መሀከል ያለው ትግል በዚህ ዙሪያ የሚደረግ ነው። ችግሩ ግን በአገራችን ምድር እውነተኛ ሳይንሳዊ ክርክር ስለማይካሄድ ጥቂት ለስልጣን የሚስገበገቡና የቲዎሪንና የሳይንስን ምርምር የሚያጥላሉ ከፍተኛ የውስጥ ለውስጥ ዘመቻ በማካሄድ ብዙዎች የአንዳንዶቻችንን አቀራረብ በሚገባ ባለመረዳት ወደ ሌላ ዝንባሌ ሲገቡና ስም ሲያጠፉ ይገኛሉ። ይህ ጉዳይ ጥንትም ያለ ወደፊትም የሚኖር በመሆኑ እኛን የስልጣኔ ተቆርቋሪዎች በፍጹም ተስፋ አያስቆርጠንም። ወደ ቁም ነገሩ እንምጣ።***

***የዛሬው አገዛዝና አማካሪዎቹ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን አለባት ሲሉና ባለፈው አስራ አራት ዓመት የነፃ ገበያን መፈክር አንግበው ተግባራዊ ሲያደርጉ ፣ እርምጃቸው ሁሉ በቲዎሪ የተደገፈ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ባይቻልም ድርጊታቸው ሁሉ በምንም ዐይነት የውስጥ ገበያን የማያዳብር ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማያስፋፋ ለመሆኑ***

የአገራችን ኢኮኖሚ ሁኔታ በቂ ምስክር ነው። ይሁንና ግን ይህ የውጭ አትኩሮቸው ደግሞ ከተሳሳተ አመለካከትና ቲዎሪ ፣ በተለይም በእንግሊዘ አገር በአዳም ስሚዝና ሪካርዶ ፣ ኢ.ኢ.አ ከ1880 ዓ.ም ጅምሮ ደግሞ ኒዎ-ክላሲክል ኢኮኖሚክስ የሚባለውና በብዙ ዩኒቨርሲቲዎች እን ደ መጽሀፍ ቅዱስ ደገማ የሚሰጠውን በንግድና በፍጆታ አጠቃቀም ላይ የተሰመረተ ኢኮኖሚክስ ትምህርት መሰረት በማድረግ ነው። በሌላ አነጋገር የእነ አዳም ስሚዝ ቲዎሪ በ16ኛው ክፍለ-ዘመን የፍጹም መንግስታት የውስጥ ገበያን ለማስፋፋት የተከተሉትን የኢን ዱስትሪ ተከላና ዕውቅ የገንዘብ ፖሊሲ እንዲሁም ደግሞ የውስጥን ገበያ ለመከላከልና ለማዳበር ያደረጉትን ከውጭ የሚመጣ የእገዳ ፖሊሲ በመዝለል የኢኮኖሚ ዕድገት በግለሰቦች ጥረትና የራስን ጥቅም በማሳደድ ላይ ብቻ ነው ብሎ በማቅረብ ያስፋፋውን ከታሪክ ጋር ያልተገናዘበ ቲዎሪ መሰረት በማድረግ ነው። ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የካፒታሊስት ዕድገት መሰረት የተጣለውና ሊዳብር የቻለው በመንግስታት ፖሊሲ አማካይነት ነው። ይህ ማለት ግን ግለሰብአዊ ድርጊትና ፈጠራ በፍጹም አልተካሄዱም ማለት አይደለም። የአዳም ስሚዝ የረቀቀ የግለሰብአዊ ድርጊት በቲዎሪ መልክ ከመነደፉና እንደመጽሀፍ ቅዱስ ዕምነት ከመወሰዱ በፊት የአውሮፓው ህዝብ አስተሳሰብ በፍልሰፍና ፣ በቲዎሪና በሳይንስ ፣ በስነ-ጽሁፍና በቲአትር እንዲሁም ደግሞ በእደ-ጥበብ መስፋፋትና በንግድ ክንውን መዳበር ሊታነጽ ችሏል። ብዙ ታሪካዊና ጠመዝማዛ ጎዳናዎችን ከተጓዘ በኋላ ነው እራሱን ማወቅ የቻለውና ወደ ግለሰብአዊ ድርጊት ለማምራት የበቃው። እንዲሁ ከሰማይ ዱብ ያለ አይደለም። ብዘዎች ኢኮኖሚስቶች አዳም ስሚዝን እንደ ዕወነተኛ የፖለቲካ ኢኮኖሚስ ፈጣሪ አድርገው ሲያቀርቡ ይህንን ታሪካዊ ሀቅ ይስታሉ። መላልሰውም በመድገም ብዙ የዋህ ሰዎችን ያሳስታሉ። ሌላው የአዳም ስሚዝ አቀራረብ ሳይንሳዊ የማይሆነው የሰው ልጅ የራሱን ጥቅም ብቻ አሳዳጅ አይደለም። እያንዳንዱ ግለሰብ ህብረተሰብአዊ አካል እንደመሆኑ መጠን በምርት ክንውንም ሆነ በንግድ ልውውጥ ሂደት ውስጥ ግኑኝነትን ይፈጥራል። የሚመረቱትም ምርቶች የብዙ ሰዎች ውጤቶች ናቸው። ከዚህም በላይ ግለሰባዊ ድርጊት ፣ ሀቀኝነትን ፣ ለተሰማሩበት ሙያ ፍቅር ማሳደርን ፣ ጥራት ያለው ምርትን ማቅረብ ፣ እራስን መቆጣጠርና ደንበኛን ማክበርና ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል። በድግምት ወይም በሰበካ የሚመጣ ሳይሆን በሳይንስና በስነ-ምግባር ላይ በተመሰረተ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው።

እነ አዳም ስሚዝ እንደዚህ ዐይነቱን ቲዎሪ ሲያዳብሩና በተለይም ደግሞ የውጭ ን ግድንና በአገሮች መሀከል የስራ ክፍፍልን መኖር አስፈላጊነትን አጥብቀው ሲያነሱ በጊዜው የእንግሊዝን ፈለግ ሊከተሉ የተነሱ አገሮችን የዕድገት መስመር ለማጨናገፍ እንደነበር እውቅ ነው። በቲዎሪያቸው መሰረት እያንዳንዱ አገር ባለው ሀብት መሰረት ፣ ማለትም ቴክኖሎጂ ያለው በቴክኖሎጂ ፣ የጥሬ ሀብትና የእርሻ ምርት ደግሞ አመቺ በሆነ ሁኔታ የሚያመርት በዚሁ መስክ ቢሰለጥንና የንግድ ልውውጥ በየአገሮች መሀከል ቢካሄድ ሁለቱም አገሮች ተጠቃሚ ይሆናሉ የሚል ነው። በመጀመሪያ አሜሪካ ከእንግሊዝ ነፃ ከወጣችና በኋላ ደግሞ በጀርመን የታወቁ ኢኮኖሚስቶችና ፈላሰፋዎች ፣ በተለይም ፍሪድሪሽ ሊስት የሚባለው የእነ አዳም ስሚዝን የተጣመመ ቲዎሪ በማሳየት ፣ ለአንድ አገር ዕድገት ዋናው መሰረት ቴክኖሎጂ ሲሆን ይህ ደግሞ በትክክለኛ ዕውቀት ላይ መመስረት እንዳለበት አረጋገጠ። በፍሪድሪሽ ሊስት ቲዎሪ መሰረት በቴክኖሎጂና በሳይንስ ላይ የተመሰረተ የኢንዱስትሪና የኢን ፍራስትራክቸር ፖሊሲ ለማካሄድ የማትችል አገር በፍጹም ነፃ አገር መመስረት አትችልም። ሁለ-ገብ ኢኮኖሚም መገንባት አትችልም። ቀደም ብለው በእነ ላይብኒዝ የዳበሩት ሳይንስ ፣ ፍልስፍናና ማቲማቲክስ ፣ ለፍሪድሪሽ ሊስት መሰረት በመሆን የፖለቲካ ኢኮኖሚውን ቲዎሪ በማዳበርና ተግባራዊ በማድረግ ለጀርመን የኢኮኖሚ መሰረት ጥሎ ለማለፍ በቅቷል።

ይህንን የእነ ፍሪድሪሽ ሊስትን ሳይንሳዊ ቲዎሪ ለመረዳት በአለፈው ሃምሳ ዐመት የተካሄደውን ዐለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍል ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። ብዙ የሶስተኛው ዐለም አገሮች በዚህ በተበላሸ ቲዎሪና በተለይም ደግሞ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማለቂያ በኋላ ተራቆ የመጣውንና በእነ ሳሙኤልሰን የተጠናቀረውን የኢኮኖሚክስ ትምህርት አሜን ብለው በመቀበላቸው ኢኮኖሚያቸው ሊውድምና ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀል ሊደርስባቸው እንደቻለ የምናየው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ያረጋግጣል። ዛሬ በአገራችን ያለውም የደፋ ቀና ፖሊሲና በአንዳንድ መሪዎቻችን የእርሻን መስክ የኢኮኖሚው ዋናው አንቀሳቃሽ

ኃይል አድርጎ ለማቅረብ መሞከር ከላይ የተጠቀሰውን የእነ አዳም ስሚዝን ቲዎሪ መሰረት በማድረግ ነው። በመጀመሪያ የእርሻ መስኩ እንዲዳብር እንኳ ቲክኖሎጂ ያስፈልጋል። እርሻን በእርሻ ማሳደግ አይቻልም። የእርሻውን መስክ በየጊዜው ለማሻሻልና የመሬቱን ምርታማነት ለማሳደግ የተሻሉ የምርት መሳሪያዎችና ምርጥ ዘሮች መቅረብ አለበቻው። ምርትን ለመሰብሰብ ፣ ለማካማቸትና ለበላተኛው ለማዳረስ እንደዚሁ የቴክኖሎጂ ዕድገት ያስፈልጋል። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታም ለማጓጓዝ እንዲሁ በትራንስፖረት መስክ ከፍተኛ ርብርቦሽ ማድረግ ያስፈልጋል። ከመኪና ይልቅ የባቡር ሀዲድና የአገር ውስጥ የባህር መንገድ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ኃይል(Energy) እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህን ለማዳበር ደግሞ ተራ ዕውቀት ሳይሆን በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ ዕውቀት ያሰፈልጋል። የአደረጃጀትንና የጥበብን ጉዳይ በየጊዜው ማሻሻል ያስፈልጋል። ከዚህ ስንነሳ የዛሪዎች መሪዎቻችን የእርሻ መፈክር የኢትየጵያን ዕድገት ጥማትና የህዝባችንን የስልጣኔ ፍላጎት ወደ ሺህ ዐመት ያራዝመዋል። ስለዚህ የአንደ አገር ዕደገት መሰረቱ በውጭ ገበያ ላይ ማትኮር ሳይሆን የውስጥ ገበያን ለማሳደግና ለማዳበር የሚደረግ ትግል መሆን አለበት። በዕውነተኛ ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ ክንውን የጥሬ ሀብት እንኳ አንድ አገር ሳይኖራት ኢኮኖሚያዋን እንደምታሳድግና የተስተካከለ ሀብረተሰብ እንደምትመሰርት ፣ ጀርመን ፣ ጃፓንና ደቡብ ኮሪያ አረጋግጠዋል።

ነገሩን ይበልጥ ለመረዳት አንዳንድ ነገሮችን መጥቀሱ ጽሁፉን የተሟላ ያደርገዋል። ቀድሞም ሆነ የዛሬዎቹ መሪዎቻችን የውጭ ምንዛሪን አስፈላጊነት አጥብቀው ሲያወሩ ወደ ውስጥ የሚዘነጉት አንድ ትልቅ ቁም ነገር አለ። ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት ከውስጥ የስራ ክፍፍል መዳበር ሲሆን ፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በአገር ውስጥ በሚሽከረከረው ገን ዘብ መያያዝ አለባቸው። የአገር ውስጥ ገንዘብ በፍጥነት ሲሽከረከርና እንደገና ወደ መዋዕለ ነዋይ ሲለወጥ ገንዘቡ ህብረተሰብአዊ ኃይል ያገኛል። በባንኮችና በተለያዩ የኢኮኖሚው ዘርፎች የሚኖሩት ግኑኝነቶች ይዳብራሉ። በእኛና በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ያለው ችግር በየአገሩ በባንክና በህዝብ ውሰጥ ያለውን ገንዘብ በተለያየ መልክ በኢኮኖሚው ውስጥ ማሽከርከር ያለመቻሉና ባንኮች ብቃት ያለው የአደረጃጀት ቴክኒክ ስለሌላቸው ነው። የውጭ ገንዘብ እናገኛለን ብሎ በውጭው የኢኮኖሚ መስክ ላይ ማትኮር የውስጥ ገበያ እንዳይዳብር ያፍናል። ሀብትን ያባክናል። ባለፉት ሃምሳ ዐመታት የታየው ይህ ድህነትን የፈለፈለ የተሳሳት የኢኮኖሚ ቲዎሪና የተሳሳተ የገንዘብ ፖሊሲ ነው።

ስለዚህ የዛሬው የመሪዎቻችን ሽር ጉድ በሳይንስና በፍልስፍና ላይ ያልተመሰረተ ሩጫ መሆኑን በመገንዘብ አገራችን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል እንዳትሆን አጥብቀን መታገል አለብን። በእነ ዓለም ባንክና በሌሎችም ዓለም አቀፋዊ ኢንስቲቱሽኖችና የኢንዱስትሪ አገሮች የሚደረግብንን ግፊት መቋቋም አለብን። በእነሱ ዕርዳታ አማካይነት ኢኮኖሚያችንን እናሳድጋለን ብለን የምንነሳ ከሆነ የታሪክ ወንጀል ፈጸምን ማለት ነው። በዚህ መስረት ባስፈለገው ቦታና ጊዜ ተገናኝተን ለኢትዮጵያ የሚበጀውን የዕደገት ፈለግ መከራከርና መንደፍ እንችላለን። እንከራከር። የሀሳብ ልውውጥ እናድርግ። ከስልጣን በፊት የቲዎሪ ፣ የሳይንስና የፍልስፍና ጥናትና ውይይት መካሄድ አለበት። መድረኩን አንዝጋ።

**ዶ/ር ፈቃዱ በቀለ ከበርሊን**